# የ Centrelink ጽ/ቤት እና በመኖሪያ ቤት የሚደረግ ቃለመጠይቅ



We speak your language ☎ 13 1202

*Centrelink Office and Home Interviews* - Amharic

Centrelink ጽ/ቤት በርከት ያሉ የአውስትራሊያ መንግሥት መምሪያዎችን በመወከል ለአውስትራሊያ ማህበረሰብ ክፍያዎችንና አገለግሎቶችን ያቀርባል።

ደንበኞች ትክክለኛ የሆነ ክፍያዎች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ Centrelink መረጃዎችን ከደንበኞች ማግኘት አለበት። ይህንን መረጃ ለማሰባሰብ የቃለመጠይቅ ማድረግ የተለመደ መንገድ ነው።

## በቃለመጠይቁ ውስጥ ስለሚኖርዎት መብቶች

ቃለመጠይቁ ሲጀመር የ Centrelink ሠራተኛ ስለቃለመጠይቁ አስፈላጊነት ምክንያቱን ያብራራልዎታል።

የቀረበልዎት ጥያቄ ካልገባዎት ወይም የ Centrelink ሠራተኛ ለምን ይህን ጥያቄ እንዳቀረበልዎት እንዲብራራልዎት መጠየቅ ይችላሉ። ክፍያውን በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ ከሆነ የመመለስ ግዴታ የለበዎትም።

የተናገሩት በርስዎ ላይ ህጋዊ እርምጃ ያስከትላል ብለው ካሰቡ ጥያቄውን ላየይመልሱ ይችላሉ። በማንኛውም ጊዜ ቃለመጠየቁን ማቆም ይችላሉ።

## በቃለመጠየቁ ውስጥ ስለሚኖርዎት ኃላፊነት

- በቀጠሮው ጊዜ መገኘት ካልቻሉ ማሳወቅ
- ለቃለመጠየቁ ጊዜ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ማዘጋጀት
- ያሉበት ሁኔታ ከተለወጠ በተቻለ መጠን ቶሎ ማሳወቅ አለብዎት፤ ለምሳሌ አድራሻ ከቀየሩ፤ ሥራ ወይም ትምህርት ከጀመሩ፤ የገቢዎት መጠን ከተለወጠ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ከሆነ።

ለሚቀርብልዎት ጥያቄ በትክክል መመለስ ጠቃሚ ይሆናል ምክንያቱም ስለርስዎ ሁኔታ የምንፈልገው መረጃ ከሌለን Centrelink ክፍያውን ሊያቆም ስለሚችል ነው።

የ Centrelink ሠራተኛ ያስሞላዎት ቅጽ ወይም የፈረሙበት ሰነድ ወይም በቴፕ የተቀዳ ቃለመጠይቅ ካለ ቅጅው እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ።

## በመኖሪያ ቤት ጉብኝት ማድረግ

የ Centrelink ሠራተኛ አንዳንዴ በመኖሪያ ቤትዎት በመምጣት ያነጋግሬል። ይህም የሚሆነው፡

- የአካል ጉድለት ወይም ህመምተኛ ከሆነ
- ወደ ጽ/ቤቱ ለመሄድ ችግር ካለብዎት እና በቤትዎ ውስጥ ለመነጋገር ከጠየቁ
- ትክክለኛ የሆነ የክፍያ መጠን ማግኘትዎን ለማረጋገጥ ግምገማ ማደድረግ ሲያስፈልግ ወይም
- የተሰጥዎት ክፍያ ትክክለኛ አይደለም ብለን ካሰብን ይሆናል።

የ Centrelink ሠራተኞች ወደ ቤትዎ በሚመጡበት ጊዜ የመታወቂያ ካርዳቸውን ማሳየት እና ጉብኝቱን እስከሚጨርሱ ድረስ ማድረግ እንዳለባቸው ነው። በመታወቂያ ካርዱ ላይ ፎቶግራፍ እና ሙሉ ስማቸው ይኖርበታል። የ Centrelink ሠራተኞች ወደ መኖሪያ ቤትዎ እንዲመጡ ከርስዎ ፍቃድ ካላገኙ መምጣት አይችሉም። በማንኛውም ጊዜ ቤትዎን ለቀወው እንዲወጡ መጠየቅ ይችላሉ።

እንግሊዝኛ ቋንቋ ካልቻሉ በቃለመጠየይቁ እንዲረዳዎት አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎት የ Centrelink ሠራተኛን መጠየቅ ይችላሉ። ይህ የነፃ አገልግሎት ነው።

ለተጨማሪ ማብራሪያ በአማርኛ ለማግኘት በስልክ ቁጥር **13 1202*** ደዉለዉ ያነጋግሩ ዌብ ሳይታችን **www.centrelink.gov.au**

** ቁጥራቸዉ በ13 የሚጀምሩ ስልክ ቁጥርች በአዉስትራሊያ ዉስጥ ከማንኛዉም ቦታ 25 ሳንቲም ብቻ ነዉ፤ በ 1800 የሚጀምሩ ስልክ ቁጥርች ሁሉ ናፃ ናቸዉ። ከሕዝብ ስልክና ከሞባይል ሲደዉሉ ክፍያዉ ከፍ ያለ ነዉ።*



Australian Government

Centrelink
giving you options